# ተስፋ ከመቁረጥ ስጋ መቁረጥ

ከሂኖክ የሺጥላ

ኑሮ ተሻሽሎዋል አሉ ... :: የት አትሉኝም? ... ኢትዮጵያ! "እንዴት?" .... በቃ! ምን ጭቅጭቅ ያስፈልጋል፣ በንዴት ኑሮው ራሱን አሻሻለ ብላችሁስ:: የስጋ ዋጋ ከረከሰ ወዲህ ሰው ስ - ሊ-ም -ቲ "የቅጥነት ሻይ " መጠጣት መጀመሩም ብዙ ድብቅ ነገር አይደለም.... እንደውም አንዳንዶች "ሁለት ወጪ ከምናወጣ፣ ለምን በሬው አስፈላጊውን ንጥረ ነገር እንዲይዝ ተደርጎ ለእርድ አይቀርብም?" በማለት ሀሳባቸውን በመሰንዘር ላይ ይገኛሉ:: ለምሳሌ መኖው ከ ቅጥነት ሻይ ቅጠል ቢዘጋጅለት በማለት:: አንዳንድ የውስጥ አዋቂዎች ደግሞ መንግስት ይህንን ነገር ያደረገው ህዝቡ "ተስፋ ከመቁረጥ ስጋ መቁረጥ" ወደሚሉት ነገር ያዘነብል እንደሆን ለመመልከት ነው ይላሉ::

"እውነታው ግን ከዚህ ይለያል" ... አሉኝ አንድ አዛውንት ... አንድ በግ ሰባት ብር ገዝተው ቆዳውን ሰባት ብር የሸጡበትን ዘመን ላለማስታወስ ከራሳቸው ጋ እየታገሉ:: ነገራቸውን ቀጠሉ ..."ድሮ ልጆች ሳለን በከተማው ላይ ውር ውር የሚሉ ጥቂት መኪኖች ሞተሮቻቸው በሚያሰሙት ድምጥ መምጣታቸውን ስናውቅ ተሩዋሩጠን እናያቸው እንደነበረ ሁሉ ... አሁን ይህ ሩጫ የበግ ወይም የፍየል ድምፅ የሰማህ እንደሆን የምታደርገው ድርጊት ነው፣ ጐረቤትክ በግ የገዛ እንደሆን፣ እባክህ አዘግይተህ እረደው ትንሽ ይጨህ ... ማለት አዲስ ነገር አይደለም... ፈርሱና አንገተቱ በበራቸው እንዲያልፍ ቦይ የሚያበጁ ብዙዎች ናቸው ... ያው ላድባሩዋ ላውጋሩዋ ማለት ነው...." አሉኝ:: ቀጠሉና ... "መንግስት ልጆቻችን በግ ምን እንደሚመስል ያውቁ ዘንድ እንደ-ስድስት ኪሎ አንበሳ ቤት ... በጎችንም በብረት ውስጥ ልናይ የምንችልበትን መንገድ ሊያዘጋጅ የገባል" ብለው ነገራቸውን ደምድመውታል::

ሰውየው ሰለስድስት ኪሎ አንበሶች ሲያነሱ ... አንድ ነገር አእምሮዬ ውስጥ ብልጭ አለ ... እነዚያ ጎን ለጎን ያሉ አንበሶች ትዝ አሉኝ .... የስድስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ አንበሶችና የስድስት ኪሎ አንበሶች ... "እንደው ለመሆኑ የሰድስት ኪሎ አንበሶች አሁንም ስጋ ነው የሚበሉት ወይስ እነሱም እንደ አጋር የዩኒቨርስቲው አንበሶቻቸው ጫት ለመዱ?" ለሃሳቤ መልሱን ሳላገኝለት ... "የሰውዬውን ንግግር ተከትሎም አንድ ወይዘሮ .... "ተውኝ ልጄ ....ነገሩ ሁሉ ድሮ ቀረ! .... አሁን በዚህ ባለፈው ገና ባልገዛ እንኩዋን እንደሁ ጠይቁ መጣሁ ለማለት ተይህ ተበግ ተራው ወርጄ ቀልቤ ያረፈበት ሙክት ወገብ ላይ መዳፌን አሳርፌ በደስታዬና በነበር ትዝታዬ ማሃከል ሰምጬ ሳለሁ ... የቆዳ ነጋዴ ወዝ ያለው የበግ ነጋዴ ... "ማዘር ምነው ሱሪ ሊያሰፉለት ነው እንዴ አለኝ?" ... ቀጠለናም ... "የዚህን በግ ወገብ ከመለካት የልጅትዎን ጭን መምታት ይቀላል አለኝ" ... ባትበላም እንኩዋ እስኪ ትመልከት በዬ ገበያ ይዤያት የወጣሁትን አንድ ፍሬ ልጅ በአይኑ እየጠቆመኝ:: በነገሩ እጅግ ስለተበሳጨሁ ...."ታዲያ ለምን እንደ- አፍሪካ ወርቅ ቤት ጌጣ-ጌጥ መስታወት ውስጥ

አትሰቅለውም?".... አልኩት በንዴት:: "እያሰብን ነው ..." አለኝ እየሳቀ:: ነገሩ የማወቅ ጉጉቴን ስለጫረው ወደመርካቶ ጎራ በዪ አንዳንድ ነገሮችን ማጥናት ጀመርኩ ... "የዋጋ ንረት ወይስ የዋጋ በረት?" ... የሚገርመው ሰዉ አሁንም ይተራመሳል .... አንድ ሱቅ ... የስግስግ ማውጫ "ስቴኪኒ" (tooth-pick) ካለመጠን ደርድሮዋል .... "ይሄ ደደብ ነጋዴ መሆን አለበት አልኩ..." ሃሳቤን ሳልጨርስ አንድ ጎርምሳ ... "ስማ ... ይሄ ሁሉ ስቴኪኒ ሰው አንጀቱን እንዲያወጣበት ነው ወይስ ..." አላስጨረሰውም ባለሱቁ ... "አይ አንዳንድ ሰዎች ለሽሮም ይጠቀሙበታል .... ካልሰማክ ከሽክላ ጋ እየተፈጨ ጠጠሩ ጥርሳቸው ውስጥ ተሰግስጎ ችግር እየፈጠረ ስለሆነ አለው ... " ሳቅ የማይጭር ግን የሚያስቅ ....የሚገርም ዘመን .... ::

ሰው እንደመንጋ በነሲብ የሚነዳበት ሃገር:: እንደፈለጋቸው የሚያደርጉዋቸው ... በሞትና በህይወት፣ በነፃነትና በባርነት ... በረሃብና በጥጋብ ... በንጉስና በሎሌ መሃከል ያለው ልዩነት ትርምስምስ ያለበት ሃገር:: የመኖር ትርጉም፣ የፍርሃት ምክንያት፣ የተስፋቢስነትና የሀሞተ ቢስነት እውነት ፍንትው ብል የሚታይባት ሃገር ... ኢትዮጵያ!

ሲገፉና ሲገፈትሩ፣ ሲናቁና ሲሰደቡ .... ሲታረዙና ሲራቡ ... በጠራራም ሲገደሉ 'በቃኝ" የማይሉ አዲስ ኢትዮጵያዊያን .... :: ታሪክን ከታሪክነት በስተቀር የተዋረሰ ምንነት በውስጡ ስለመያዙ የሚጠራጠሩ ... የመሩዋቸው የሚገዙዋቸው የራስ ፍንግሎች ...:: "እየሞቱ መኖር ማሰብ በምን ተሽሎ ይሆን ... ብዙ ሰው ዝምታን የመረጠው?" .... ይሄ ነገር ከፍርሃትም ይለያል ... ፍርሃት በተራበና መራብን በሚፈራ መሃከል እንዴት እኩል ሊሆን ይችላል? ፍርሃት በሞተና ሞትን በሚፈራ ሰውስ አይን እንዴት ኢኩል ይታያል? ....

... ይገርመኛል! ....